አንዳችሁ ዉዱእ አድርጎ ኹፎቹን የለበሰ እንደሆነ እነርሱን እንደለበሰ ይስገድ። በነርሱም ላይ ያብስና ከዚያም ለጀናባ ካልሆነ በቀር ከፈለገ አያውልቃቸው።

ከአነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም)
የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ ዉዱእ አድርጎ ኹፎቹን የለበሰ እንደሆነ እነርሱን እንደለበሰ ይስገድ። በነርሱም ላይ ያብስና ከዚያም ለጀናባ ካልሆነ በቀር ከፈለገ አያውልቃቸው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ዳረቁጥኒይ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አንድ ሙስሊም ውዱእ አድርጎ ኹፎቹን ከለበሰ በኋላ ዉዱኡን አፍርሶ ዉዱእ ማድረግ ከፈለገ ኹፎቹ ላይ ማበስ እንደሚችል፣ ለተገደቡ ጊዜያትም ሳያወልቃቸው እነርሱን እንደለበሰ መስገድ እንደሚችል ገለፁ። ጀናባ ካጋጠመው ግን ኹፉን አውልቆ የመታጠብ ግዴታ አለበት።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/8392